# ደጋግሞ መዋሸት ያቀላል እንጂ አያስከብርም (የግል አስተያየት)

ከማንበግሮት ታፈሰ
ቶሮንቶ፣ ካናዳ

ጥቅምት 7 ቀን 2000 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ የሰሜን አሜሪካ ልዑካን ቡድን መግለጫ አውጥቷል። መግለጫው የሚቀጥሉትን ነጥቦች አካቷል።

1. ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ቡድኑን በሊቀመንበርነታቸው እንዲመሩና ተልእኮውንም እንዲወጡ ከኢትዮጵያ ከመነሳቱ በፊትና እዚህም ከመጣ ጀምሮ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ጠይቂቸው እሳቸው ግን ጥሪውን እስካሁን አልተቀበሉትም፣
2. ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የራሳቸውን አጀንዳ አውጥተው በቅንጅት ስም ተግባራዊ በማድረግ ላይ ናቸው፣
3. ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የራሳቸውን አጀንዳ ተግባራዊ የሚያደርጉትም የሚመለከታቸው የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባላት መክረው ባፈረሱትና መፍረሱንም በፊርማቸው ባረጋገጡት የቅንጅት አለም አቀፍ ምክር ቤት እያለ እራሱን በሚጠራ አካል አማካይነት ነው፣
4. ከላዕላይ ምክር ቤት አካል ውሳኔ ውጪ የምክር ቤት አባል የሆኑም ያልሆኑም ሰዎችን በራሳቸው ፈቃድ እያስመጡ በቡድናቸው ውስጥ በአባልነት እንዲንቀሳቀሱ እያደረጉ ነው፣
5. በቅንጅት ልዑካን ውስጥ የሚታየው ጊዜያዊ ችግር በሥልጣን ሽኩቻ የተፈጠረ ሳይሆን
    ሀ/ ዲሞክራሲያዊ አደረጃጀትና
    ለ/ የጋራ አመራር ሥነስርዓትን በመቀበልና ባለመቀበል መካከል ባለው ልዩነት ነው
    ሐ/ ይህንን ቅንጅት ባለው ሕገ ደንብ መሠረት አገር ውስጥ ውሳኔ ይሰጥበታል
6. የልዑካን ቡድኑ የተሰጠውን ተልእኮ በአግባቡ ለማከናወን ይቀጥላል

መግለጫው ስድስት ዋና ነጥቦችን የያዘ ሲሆን ስድስቱም ነጥቦች ውሸቶች ናቸው። ውሸት መሆናቸውን ሕዝብ ቢያውቅም፣ እያንዳንዱን ነጥብ ምን ውሸት እንደሚያደርገው ማሳየት አስፈላጊ ነው።

1. ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ቡድኑን በሊቀመንበርነታቸው አልመራም አላሉም። ይህ ፍጹም ውሸት ነው። እሳቸው ያሉት ከጉዞው በፊት በአገር ቤት መሠራት ያለባቸውን ጉዳዮች እንሥራና ከዚያ በኋላ የውጭውን ጉዞ እናድርግ ነው። ቡድኑ እሳቸው ወደ ሰሜን አሜሪካ በመሪነት እንዲመጡ አልፈለገም። ቪዛም እንዳይሰጣቸው ትልቅ ሚና ተጫውቷል።

2. ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የራሳቸው አጀንዳ የላቸውም ይህ ፍጹም ውሸት ነው። ኖሯቸውም አያውቅም። ነገር ግን ደጋግመው የሚናገሩትና የሚለፉለትም አንድ አጀንዳ አላቸው። ይህም አጀንዳ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ከወያኔ ጥፋት፣ በደልና ግፍ ነጻ ማውጣት ነው። በዚህም ትልቅና ክቡር አጀንዳቸው እናከብራቸዋለን እንኮራባቸዋለን። እንከተላቸዋለንም።

3. የቅንጅት ዓለም አቀፍ ምክር ቤት በክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ፊርማ አልፈረሰም። ይህ ፍጹም ውሸት ነው። በእሳቸው ፊርማ የመጣውን ደብዳቤ እረጋ ብሎ በቅጡ ማንበብ ያስፈልጋል። ደብዳቤው በከፊል እንዲህ ይላል፣ "....<u>በመሆኑም ይህ መልዕክት ከደረሳችሁ ጊዜ ጀምሮ እኛን በመወከል ትሰጡ የነበረው የፖለቲካ አመራር መቋረጡን እያሳወቅን፣ ይህንን ሸክም ለረጅም ጊዜ ይዛችሁ በብቃት በመወጣታችሁ ለእናንተ ያለንን አክብሮትና አድናቆት እንገልጻለን።</u>" የፈረሰው ለረጂም ጊዜ ቅንጅትን ለመምራት ተወክያለሁ ሲልና ቅንጅትን ለመከፋፈልና ለማፍረስ ሲሯሯጡ የነበረው የነብርሃነ መዋ፣ የአንዳርጋቸው ጽጌና የዶ/ር ሞገስ ገብረማርያም ቡድን እንጂ <u>አዲስ የተቋቋመው የቅንጅት ዓለም አቀፍ ምክር ቤት አይደለም።</u> እናንተ እርሱን ፈርሷል የምትሉት የናንተ የመከፋፈልና የማፍረስ አጀንዳ ስለማያራምድ ነው። የእናንተም መልዕክተኞች ከዚህ አካል ራሳቸውን ያገለሉት የመከፋፈልና

የማፍረስ አጀንዳቸውን ማካሄድ እንደማይችሉ ስለተረዱ ነው። የቅንጅት ዓለም አቀፍ ምክር ቤት አዲስ የተቋቋመ አካል ከመሆኑም በላይ ለረጂም ጊዜ የፖለቲካ አመራር ሲሰጥም አልነበረም። ይህንን ስናደርግ ቆየን ያሉት እነ ብርሃን፣ አንዳርጋቸውና ዶ/ር ሞገስ ናቸው እንጂ የአዲሱ ምክር ቤት አባላት አይደሉም። ስለዚህ በማያወላውል መልእክት የፈረሰው የቅንጅት ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ እያለ ራሱን ሲጠራ የነበረው ቡድን ነው።

4. ከላእላይ ምክር ቤት አካል ውሳኔ ውጪ የምክር ቤት አባል የሆነም ያልሆነም ሰዎች በራሳቸው ፈቃድ አላስመጡም። ይህ ፍጹም ውሸት ነው። ይሁን እንጂ የመጡት ሰዎች እንደነሱ የተመረጡና የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ናቸው። አሜሪካ የመምጣት ያለመምጣትም ሙሉ መብት አላቸው። ከዚያም አልፎ ቅንጅትን ለመከፋፈልና ለማዳከም ቀና ደፋ ሲሉ እነርሱ አጃቸውን አጣምረው ቆመው እንዲመለከቷቸው የሚጠብቁ ይመስላል። እነዚህ ሐቀኛ የቅንጅት ተመራጮችና የአመራር አባላት የለፉለት፣ የታሰሩለትና የተንገላቱለት ድርጅት አደጋ ላይ ሲወድቅ የማዳንና የመከላከል ሃላፊነት አለባቸው። ይህንን በማድረጋቸው እናከብራቸዋለን። እንኮራባቸዋለን።

5. በቅንጅት ልዑካን ውስጥ የሚታየው ጊዜያዊ ችግር የሥልጣን ሽኩቻ አይደለም ይላል። ይህ ፍጹም ውሸት ነው። የችግሩ መነሻ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የተጠናወተው የሥልጣን ጥም ነው። እርሱ ይንን ጥሙን በሴራና በአድማ እውን ለማድረግ ነው የፈለገው። ዶክተር ብርሃኑ ሥልጣንን የሚሻው የወያኔን እድሜ ለማራዘምና የእርሱን የንዋይ ፍላጎት ለማርካት እንጂ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ከወያኔ ነጻ ለማድረግ አይደለም። የሰውዬውን የእስካሁን የሕይወት ጉዞ የተከታተለ ሁሉ ይህንን በትክክል ሊረዳ ይችላል። አንድ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ያልተረዳው ትልቅ ቁም ነገር አለ ይህም እውነተኛ መሪነት የሚገኘው ከመልካም ተግባርና ከሕዝብ ፈቃድ እንጂ ከመጋረጃ በኋላ ሆኖ በሚጠነሰስ ሴራና ተንኮል አይደለም። ዶክተር ብርሃኑና የሱ ቀንደኛ መልእክቶች ያዋጣናል ብለው የያዙት ሴራና ተንኮል ሁለት ሥልቶች አሉት፤

   አንደኛው ሥልት፣ ዲሞክራሲያዊ አደረጃጀት የሚለው ነው። ይህ ሥልት ብቅ ካለ ቆይቷል። ብቅ ያለውም በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አስተዋዋቂነት ነው። ዋናው የቅንጅት ኢንተርናሽናል ሊደርሽፕ አርክቴክ ሆኖ ቅንጅትን ለመከፋፈልና ለማዳከም ፕላኑን ይፋ ሲያደርግ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ዲሞክራሲያዊ አደረጃጀት መከተል አለባቸው ነው ያለው። በነገራችን ላይ ዲሞክራሲያዊ አደረጃጀት ኮሚኒስቶች ዲሞክራቲክ ሴንትራሊዝም የሚሉት የፓርቲና የሕዝብ መቆጣጠሪያ ሰንሰለት ነው። እኛ የምናውቀው ሊበራል ዲሞክራሲና የነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ዲሞክራሲያዊ አደረጃጀት ፍጹም ተቃራኒዎች ናቸው። በአጠቃላይ ዲሞክራሲያዊ አደረጃጀት የኮሚኒዝም ፍልስፍናና መርሆ ሲሆን ከምዕራባውያን ዲሞክራሲ ጋር በኃይል ይቃረናል። በአሰራር ደረጃ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ አደረጃጀት ማለት የፓርቲውን አካላት በሙሉ በታማኝ ካድሬዎቻቸው አስይዞ ጥቂቶች የሚፈልጉትን አጀንዳ ማካሄድና ማከናወን ማለት ነው።

   ምሳሌ ለመስጠት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ዲሞክራሲያዊ አደረጃጀትን ወደ ቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ይዞ ሲመጣ ሊያደርግ የሞከረውን እንመልከት። እንደሚታወቀው ሁሉ በሰሜን አሜሪካም ይህን በአውሮፓ ለብዙ ጊዜ በኢትዮጵያችን ዲሞክራሲና የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን በራሳቸው አነሳሽነት ተደራጅተው ሲታገሉ የቆዩት በመጀመሪያ የመኢሕድ፣ ቀጥሎ የመኢአድ ደጋፊዎች ነበሩ። ቅንጅትም ሲፈጠር እራሳቸውን የቅንጅት የድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች አድርገው ጥንት ያደርጉት የነበረውን ሁለ ገብ እርዳታ መስጠት ቀጠሉ። እነዚህ ድርጅቶች የአንድ ሰው ወይንም ቡድን "ቲፎዞ" ሆነው ሳይሆን የሚታገሉት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ነው። በዚህ መልኩ እነዚህ ድርጅቶች የአንዳርጋቸውንና ያዛገፉን አጀንዳ ለማራመድ ፈቃደኛ አይሆኑም። ከዚያም አልፎ ይቃወማሉ። ይህን ችግር ለመወጣትና የቅንጅትን የድጋፍ ደርጅቶች ለመቆጣጠር የተነደፈው ፕላን ያሰለጠኗቸውንና የኛ ናቸው የሚሏቸውን ካድሬዎች በየድጋፍ ድርጅቶች ውስጥ እንዲገቡ ካደረጉ በኋላ የኮሚኒስቶች ምርጫ አካሂደው የድጋፍ

ድርጅቶችን መቆጣጠርና ከዚያ በኋላ ድርጅቱን ለወያኔ ገጸበረከት ማስረከብና አስፈላጊውን ሽልማት መቀበል ነበር። በብዙ ትግል የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ከዋሽንግተን ዲሲና ለንደን (ኢንግላንድ) በስተቀር ነጻነታቸውን ጠብቀው እዚህ ደርሰዋል። አሁን ደግሞ ቅንጅትን ሊከፋፍልና ሊያዳክም የሚንቀሳቀሰው የአምስት ሰው ቡድን ያለው ችግር ዲሞክራሲያዊ አደረጃጀትን እንቀበላለንና አንቀበልም በሚለው መሀል ነው አለን። አሁን የዚህ ቡድን ዓላማና ፕላን ምን እንደሆነ ግልጽ ሆኗል። ለካስ አቶ አንዳርጋቸው ልባችንን በዲሞክራሲያዊ አደረጃጀት እያለ ሲያወልቀን የነበረው በተሰጠው ትእዛዝ ኖሯል። ሕዝብ ነጻ የሚያደርግ ስነሥርዓት እንጂ ሕዝብን ባርነት ውስጥ የሚያስገባ ስነ ሥርዓት ፈጽሞ ኢትዮጵያችን ውስጥ ተመልሶ አይመጣም።

እስካሁንም ወደፊትም የምናምነው ግልጽ በሆነ ውይይት እያንዳንዱ ሰው ባመነበትና በሚፈልገው ዓይነት ድምጽ ሰጥቶ በድምጽ ብልጫ ውሳኔ መመራት እንጂ ጥቂቶች ከታማኝ ካድሬዎቻቸው ጋር ሸርበው በማጭበርበር በድምጽ ብልጫ ምርጫ አሸንፈን እያሉ የሚያታልሉበት የኮሚኒስቶች ትያትር አይደለም። አንቀበልም። ይህንን አይን ያጣ ማጭበርበርና የሕዝብ አደራ ክደት ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውልና ሌሎች እውነተኛ የቅንጅት ተመራጮችና የአመራር አባላት ብቻ ሳይሆኑ እኛም እንታገላለን፣ እንቃወማለን። ዲሞክራሲያዊ አደረጃጀትን ከአመጣችሁበት ቦታ መልሰው ያኑሩት። ከዚህ በኋላ እሱ ቦታ የለውም። በእርሱም ተጠቅሜ ሥልጣን እይዛለሁ የሚል ዘመኑ ያለፈበት ፍጡር ነው። እውነተኛ አደረጃጀትን ለማወቅ ከፈለጉ ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ኢትዮጵያ ውስጥ የሠሩትን ተአምር መመልከት ተገቢ ነው። ለነገሩ ከአዲስ አበባ ክልል እርቀው ያልሄዱ ሊያውቁት አይችሉም።

ሁለተኛው ስልት የጋራ አመራር ሥነሥርዓት የሚሉት ነው። በዚህ በሃያ አንደኛው ሺህ ክፍለ ዘመን የጋራ አመራር የሚከተል ፓርቲም አገርም የለም። አስተሳቡ እራሱ ቀጥተኛነትና ግልጽነት የለውም። ብዙ ሀተታ ከማድረግ እንቆጠብና አምስቱ የልዑካን ቡድንም ይሁን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የጋራ አመራር እያሉ ሲናገሩ ምን ማለት ፈልገው ነው? የሚለውን እንመርምር። ዋናው አላማቸው ቅንጅት አንድ መሪ የለውም ቅንጅት ያለው ብዙ መሪዎች ነው ለማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ብቻ የቅንጅት መሪ አይደሉም፣ ከብዙ መሪዎች አንዱ እንጂ ። እንዲህ ከሆነ ደግሞ መሪው ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ፓርቲው የሠጣቸውን የመሪነት ሥልጣን ተጠቅመው አስፈላጊ ውሳኔዎች አያደርጉም ማለት ነው። ይህ የነሱ የጋራ አመራር ምኞትና ሤራ እንጂ የፓርቲውም የላዕላይ ምክር ቤቱም ውሳኔ አይደለም።

ይህን የጋራ አመራር ተብዬ ቡድኑ የሚፈልገው ሥልጣን ከክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ለመንጠቅ እጠቀምበታለሁ ብሎ እንጂ እሥራ ላይ የማይውል ሀሳብ እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል። የጋራ አመራር ከሚለው ቡድን ውስጥ ዶክተር ብርሃኑ ነጋን በማሞገስና በማወደስ ከቡድኑ ውስጥ መሪ አድርጎ ለማውጣት ነው፡ ይህንን ለማድረግ ሥራው ከተጀመረ ቆይቷል። ግሩም ድንቅ ደራሲ በማለት ብዙ ፕሮፓጋንዳ ተካሂዷል። የዶክተር ብርሃኑን "ከልት" ለመፍጠር ብዙ ትያትር ተካሂዷል እየተካሄደም ነው። ወይዘሪት ብርቱካንንም ያልሆነችውን ነች፣ ያልጻፈችውን ጻፈች ተብሎ ተነግሮአል። የጣምራ "ከልት" ለመፍጠር ብዙ ተለፍቶበታል። ይህን ለማድረግ የተሯሯጡት ትዝብት አተረፉ እንጂ አንዳችም ያገኙት ጥቅም የለም። ይህ ቡድን አሁን የጋራ አመራር እያለ የሚሳለቅብን ዶክተር ብርሃኑ ተሳክቶለት መሪነቱን ቢያገኝ፣ መጀመሪያ የጋራ አመራርን የሚኮንነው እሱ ነው። ያም ሆነ ይህ በእንደዚህ ያለ ሰንካላና የማይሠራ ሀሳብ እኛን ማታለል መሞከር ከንቀትም አልፎ ትእቢተኛነትን ያንጸባርቃል። ስለ መሪነትና አመራር የበሰለና የጠለቀ ተመክሮ እንዳለን መገመት በተገባቸው ነበር። በነገራችሁ ላይ አንድ መሪ መሪነቱ የሚታወቀው በሚያራምዳቸው የአገርና የሕዝብ አጀንዳዎች ሲሆን፣ የሚመራውም ሕዝብ ያለአንዳች ግፊትና ተጽእኖ መሪዬ ብሎ ሲቀበለውና ሲከተለው ነው። መሪውም የያዘውን የሕዝብና የአገር አጀንዳ ሳያወላውል በጥንካሬ ወደፊት ያራምዳል። ላልተሳካውና ለጎደለው ኃላፊነት ይወስዳል። የጋራ አመራር ስልት ስልጣን

ይዞ ኃላፊነት ሳይቀበል በሕዝብ ትከሻ ላይ ተንዘራፍጦ ሊቀልድ በሚፈልግ ቡድን የሚፈለግ የማጭበርበሪያ መንገድ ነው።

ቅንጅት የሚመራው በጋራ አመራርና አሰራር ነው ከተባለ፤ አልተባለም እንጂ፤ ይህንን አሰራር የላዕላይ ምክር ቤት ተወያይቶ አጽድቆታል? ተወያይቶ ካጸደቀው የጋራ አመራሩ አባላት እነማን ናቸው? የአመራር ሥራቸውስ በምን መልክ ነው የሚያካሂዱት? አንድ ተጠሪስ አላቸው? ያስ ተጠሪ ማነው? ምን፣ ምን የማድረግ መብትና ግዴታ አለበት? ይህንን ሁሉ ከወሰነ የፕሬዚዳንቱ የክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ሥልጣንና ግዴታ ለማን ተዛወረ? እሳቸውስ ምን እንዲሰሩ ተወሰነ? እረ ለመሆኑ ይህን ውሳኔ የላዕላይ ምክር ቤቱ መቼ ተሰብስቦ ነው የወሰነው? ስብሰባውን ማን መራው? ቃለ ጉባኤስ አለው ወይ?

ሌላው አንገብጋቢ ጥያቄ ደግሞ የላዕላይ ምክር ቤት ተሰብስቦ ይህን ውሳኔ ሲያደርግ የክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል መሪነት ምን፣ ምን ጉድለትና ድክመት ተገኘበት? ከተገኘም ጉድለቶቹና ድክመቶቹ ምን፣ ምን ናቸው? የክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል አመራር የተገኙበትን ጉድለቶችና ድክመቶች እንዲያሻሽልና እንዲያርም ተጠይቆ ሊያርምና ሊያሻሽል አልቻለም ማለት ነው?

የጋራ አመራሩ በክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል አመራር ላይ የታዩትን ጉድለቶችና ድክመቶች እንዴት አድርጎ እንደሚያሻሽል ተዘርዝሮ ተገልጧል? ለአሰራሩስ የተሰጠው ገደብና ሥልጣን እስከየትና እንዴት ነው? ይህ ከሆነ የጋራ አመራር አማኝ ቡድን ለምንድነው ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውልን መሪው አድርጎ ወደ አሜሪካ ሊመጣ የወሰነው? ከመጣስ በኋላ በአንድ በኩል የመከፋፈል ሥራውን እየሠራ በሌላ በኩል ደግሞ ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ቡድኑን እንዲመሩ ሲጠየቁ እምቢ አሉ ይላል። ይሄ በአንድ አፍ ሁለት ምላስ ምንድነው ትርጉሙ?

እነኝህ የጋራ አመራር ተሚጋቾች እዚህ ለተጠየቁት ጥያቄዎች ምንም ዓይነት መልስ ሳይሰጡ ነው የቅንጅት አመራር የጋራ አመራር ነው እያሉ የሚያፌዙብን። የሌለና ያልሆነን ነገር ፈጥረው ልዩነቱን የፈጠረው ይህ ነው ይሉናል። በመሠረቱ ሥልጣንን በሥራ ከመተርጎም በፊት ሥልጣንን ማግኘት ይቀድማል። ሰዎቹ የጋራ አመራር ሥልጣን ሳይኖራቸው ነው የጋራ አመራር ሥልጣን ለመጠቀም የሚሹት። ይህንን የትም የማያደርስ ሙግት ትተው አነሳሳችን የቅንጅትን ዓላማና ግብ ማለትም የኢትዮጵያን ሕዝብ የዲሞክራሲ ትግል አዳክመን የወያኔ ታማኝና የይስሙላ ተቃዋሚ ሆነን በምናገኘው ድጎማ እየተንደላቀቅን መኖር ነው የምንሻው ቢሉ በግልጽነታቸውና በአቋማቸው እንኳ ቢሆን እናከብራቸው ነበር። ነገር ግን ቅንጅትን ተገን አድርገው ቅንጅትን ለማደከም፣ ለመከፋፈል በመሞከራቸው አፍረንባቸዋል፤ አስቆጥተውናል። እራስን ማረምና ማስተካከል ጨዋነት ነው። ጨዋነት ደግሞ የኢትዮጵያኖች ልዩ አርማችን ነው። የእውነተኛ መሪ ስራ ቢሰሩ እኮ እነርሱ ሳይነግሩን መሪዎቻችን ብለን እንቀበላቸው ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ ዓላማና ግብ እያዳከሙ ከጠላቱ ጋር እያደሙ መሪዎች ነን ሲሉን ደፍረውናል ንቀውናልም። ይህ ደግሞ በጣም አናዶናል አስቆጥቶናል። በዚህ አሳፋሪ ስራቸው ምሳሌው አቶ መለሰ ዜናዊ መሆናቸውን እንገምታለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአቶ መለሰ ዜናዊ የሰጠውን መሪነትና አክብሮት ለእነርሱም እንደሚሰጣቸው አንጠራጠርም።

የልዑካኑ ቡድን የተሠጠውን ተልእኮ በአግባቡ በመወጣት ላይ አይደለም። ይህ ፍጹም ውሸት ነው፡ እውነቱ ግን ቡድኑ ቅንጅትን የመከፋፈል፣ የማዳከም ተግባሩን በማራመድ ላይ ነው። በዚህ ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አዝኖበታል፣ ተቆጥቷል። ሕዝብን የሚንቅ አወዳደቁ አያምርም። የእንተም አወዳደቅ አያምርም። ወድቃችሁም አትነሱም።